# ቀላል እውነታዎች
# ለአዲስ አማኝ

**(ጥያቄዎች እና መልሶች)**

ሁለተኛ እትም
እትም 2.0

## መቅድም

ለበርካታ አመታት፤የእግዚአብሔር ሰዎች ለአዲስ አማኞች አስፈላጊ የሆኑ እውነቶችን ለማስተማር የጥያቄዎች እና መልሶች ስብስብ ይጠቀሙ ነበር፡፡ይህ መጽሐፍ ኢየሱስን ለሚከተሉ የአዲሱ ትውልድ ሰዎች እነዚህን አስፈላጊ እውነታዎች ያቀርባል፡፡

ይህ መጽሐፍ 144 ጥያቄዎችን እና መልሶችን ይዟል፡፡ከእያንዳንዱ ጥያቄ በኋላ ወዲያው መልሱ ይከተላል፡፡እያንዳንዱ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተመረጡ ጥቅሶችን ይዟል፡፡እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የመጽሐፉን ርዕስ ያካትታል (ለምሳሌ፤ዘፍጥረት)፡፡ የመጽሐፉ ስም ጥቅሱ በሚገኝበት በምዕራፉ ይከተላል (ለምሳሌ፤ምዕራፍ 2)፡፡ይህም በጥቅሱ ወይም ጥቅሱ በሚገኝበት ስፍራ ይከተላል (ለምሳ፤ቁጥር 3)፡፡ስለዚህ፤ዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት፤ቁጥር ሦስት ይህን ይመስላል፤ ዘፍጥረት 2፡3

**እትም በ:**
www.clearandsimplemedia.org

**የዚህን መጽሐፍ ኤሌክትሮኒክ እትም ለማግኘት፤የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ:**
www.asimpleword.org

**ትርጉም በ:**
www.christian-translation.com

አንዳንድ መልሶች ያልተሟላ አረፍተነገር ይይዛሉ (ለምሳሌ፡ጥ.4)

**ክፍል አንድ**
**እግዚአብሔር እና ሰው**
ጥያቄዎች ከ1 እስከ 26

**ክፍል ሁለት**
**ሐጢያት* እና ህግ***
ጥያቄዎች ከ27 እስከ 62

**ክፍል ሦስት**
**ክርስቶስ እና ደህንነት***
ጥቄዎች ከ63 እስከ 90

**ክፍል አራት**
**መንፈስ እና ቤተክርስቲያን**
ጥያቄዎች ከ91 እስከ 117

**ክፍል አምስት**
ጸሎት እና ተስፋ
ጥያቄዎች ከ118 እስከ 144

ይህን ምልክት* በሚመለከቱ ጊዜ፤ምልክቱ ያለበት ቃል በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ በሚገኘው በቃላት ዝርዝር ውስጥ መገኘቱን እየነገረዎት ነው፡፡

## ክፍል አንድ
## እግዚአብሔር እና ሰው

Q.1 የፈጠረህ ማን ነው?

**A. እግዚአብሔር ፈጠረኝ፡፡**

ዘፍጥረት 1:26-27; ዘፍጥረት 2:7; ሐዋ 17:26

**Q.1** እግዚአብሔር ሌላ ምን ፈጠረ?

**A. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ፈጥሯል፡፡**

ዘፍጥረት 1:31; መዝ 33:6-9; ቆላ 1:16-17

**Q.2** እግዚአብሔር አንተን እና ሁሉንም ነገሮች ለምን ፈጠረ?

A. **እግዚአብሔር እኔን እና ሁሉንም ነገሮች የፈጠረው ለእራሱ ክብር ነው***.

መዝ 19:1; ኢሳ 43:7; 1 ቆሮ 10:31

**Q.3** ለእግዚአብሔር ክብርን* እንዴት ትሰጣለህ?

A. **እግዚአብሔርን ስወደው እና ስታመነው ለእግዚአብሔር ክብር* እየሰጠሁ ነው፡፡**

ማቴ 5:16; ዮሐ 14:21; 1ኛ ዮሐ 5:3

**Q.4** ለምን ለእግዚአብሔር ክብር* ትሰጣለህ?

A. **ምክንያቱም እሱ ፈጥሮኛል ደግሞም ይጠብቀኛል፡፡**

መዝ 145:9; 1ኛ ጴጥ 5:7; ራዕይ 4:11

**Q.5** ምን ያህል አምላክ አለ?

A. **ያለው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡**

ዘዳግም 6:4; ኢሳ 45:5; ኤር 10:10

**Q.6** ይህ አንድ እግዚአብሔር በስንት ስብዕና ይኖራል?

A. **እግዚአብሔር በሦስት ስብዕና ይኖራል**

ማቴ 3:16-17; ዮሐ 5:23; ዮሐ 10:30; ዮሐ 15:26

**Q.7** እነማን ናቸው?

A. **አብ**, ወልድ, እና መንፈስ ቅዱስ*.

ማቴ 28:19; 2ኛ ቆሮ 13:14; 1 ጴጥ 1:2

Q.8 እግዚአብሔር ምንድ ነው?
A. **እግዚአብሔር መንፈስ ነው***፡፡ እሱ እንደ ሰዎች ስጋ የለውም፡፡
ዮሐ 4:24; 2ኛ ቆሮ 3:17; 1ኛ ጢሞ 1:17

Q.9 እግዚአብሔር መጀመሪያ ነበረው?
A. **አልነበረውም**፤እግዚአብሔር ሁልጊዜም ነበር፤እግዚአብሔር ሁልጊዜም ይኖራል፡፡
ዘጸአት 3:14; መዝ 90:2; ኢሳ 40:28

Q.10 እግዚአብሔር ይቀየራል?
A. **አይቀየርም**፤እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያው ነው፡፡
መዝ 102:26-27; ሚል 3:6; ዕብራውያን 13:8

Q.11 እግዚአብሔር ያለው የት ነው?
A. **እግዚአብሔር ሁሉም ቦታ ይገኛል**፡፡
መዝ 139:7-12; ኤር 23:23-24; ሐዋ 17:27-28

Q.12 እግዚአብሔርን ማየት ትችላለህን?
A. **አልችልም**፤እግዚአብሔርን ማየት አልችልም፤ነገር ግን እሱ ሁልጊዜ እኔን ያየኛል፡፡
መዝ 33:13-15; ምሳሌ 5:21; ዮሐ 1:18; 1ኛ ጢሞ 1:17

Q.13 እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ያውቃል?
A. **አዎ**፤እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ያውቃል፡፡ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ልሰውር አልችልም፡፡
1ኛ ሳሙ 2:3; ምሳሌ 15:3; ዕብራውያን 4:13

Q.14 እግዚአብሔር ሁሉን ነገሮች ሊያደርግ ይችላልን?
A. **አዎ**፤እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚፈልጋቸውን ቅዱስ ነገሮች ማድረግ ይችላል፡፡
ኢሳ 46:9-10; ዳንኤል 4:34-35; ኤፌ 1:11

Q.15 እግዚአብሔርን ማወቅ፤መውደድ እና መታዘዝ የምማረው የት ነው?
A. **እግዚአብሔር በቃሉ እንዴት እንደማውቀው፤እንደምታመነው፤እንደምወደው እና እንደምታዘዘው አሳይቶኛል፡፡**
መዝ 119:104-105; ዮሐ 20:30-31; 2ኛ ጢሞ 3:15

**Q.16** መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምርህ ምንድ ነው?
**A. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር እውነት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን የማዳን እቅዱ ያስተምረኛል፡፡እንዲሁም ስለ እኔ እውነት ያስተምረኛል፡፡**
መዝ 119:159-160; ዮሐ 17:17; 2ኛ ጢሞ 3:14-17

**Q.17** መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ማን ነው?
**A. በመንፈስ ቅዱስ* በተመሩ እና በተማሩ ሰዎች**
2ኛ ጴጥ 1:20-21; 2ኛ ጴጥ 3:15-16

**Q.18** የእኛ የመጀመሪያ ወላጆች እነማን ነበሩ?
**A. አዳም እና ሔዋን፡፡**
ዘፍጥረት 3:20; ዘፍጥረት 5:1-2

**Q.19** እግዚአብሔር የመጀመሪያ ወላጆቻችንን እንዴት ሰራቸው?
**A. እግዚአብሔር የአዳምን ስጋ ከምድር አፈር አበጀው፡፡ሔዋንን ደግሞ ከአዳም ስጋ ፈጠራት፡፡**
ዘፍጥረት 2:7; ዘፍጥረት 2:21-23; ዘፍጥረት 3:19; መዝ 103:14

**Q.20** አዳም እና ሔዋን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ከሌሎች ነገሮች እንዴት የተለዩ ሆኑ?
A. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በራሱ አምሳል ፈጥሯቸዋልና፡፡
ዘፍጥረት 1:26-27

**Q.21** የእግዚአብሔርን መልክ በአዳም እና ሔዋን ውስጥ እንዴት ማየት እንችላለን?
**A. እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ እንዲገዙ ትዕዛዝ ሰጣቸው፡፡እነሱ እውነት የሆነውን መረዳት ይችላሉ፡፡ትክክለኛውን መውደድ ይችላሉ፡፡በሚያምረው መደሰት ይችላሉ፡፡እግዚአብሔርን የሚየስደስተውን ማድረግ ይችላሉ፡፡ከእግዚአብሔር ጋር እና እርስ በእርሳቸው መነጋገር ይችላሉ፡፡**
ዘፍጥረት 1:26-27; ዘፍጥረት 2:7-9; መዝ 147:10-11; ፊሊ 4:8

**Q.22** እግዚአብሔር ከስጋ ሌላ ለአዳም እና ሔዋን ምን ሰጣቸው?
**A. እግዚአብሔር የማይሞት ነፍስ* ሰጣቸው፡፡**
ዘፍጥረት 2:7; ዘዳግም 6:5; መክብብ 12:7; ማቴዎስ 16:26

**Q.23** ነፍስ* እንዲሁም ስጋ አለህን?
**A. አዎ፤** የማይሞት ነፍስ* አለኝ፡፡
ዘካሪያስ 12:1; ሐዋ 7:59; 2ኛ ቆሮ 5:8

**Q.24** እግዚአብሔር አዳም እና ሄዋንን ሲፈጥራቸው ምን ይመስሉ ነበር?
**A. እግዚአብሔር ቅዱስ* እና ደስተኛ አደረጋቸው፡፡እሱ ባዘጋጀላቸው የአትክልት ስፍራ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖሩ ነበር፡፡**
ዘፍጥረት 1:26-28; ዘፍጥረት 2:15-17; ዘፍጥረት 2:25; መዝ 8:4-8

**Q.25** እግዚአብሔር ከአዳም እና ሔዋን ምን ይፈልግ ነበር?
**A. እግዚአብሔር ፍጹም እንዲታመኑት እና እንዲታዘዙት ይፈልግ ነበር፡፡**
ዘፍጥት 2:15-17; መዝ 8:4-8

## ክፍል ሁለት
## ሐጢያት እና ህግ

**Q.26** አዳምና ሄዋን እግዚአብሔርን ታዘው ቅዱስ* እና ደስኞች ሆነው ኖሩ?
**A. አልኖሩም፤** አልታዘዙም፡፡ሐጢያትን መስራትን መረጡ፡፡
ዘፍጥረት 3:6-8

**Q.27** ሐጢያት ምንድ ነው*?
**A. ሐጢያት ማለት እግዚአብሔር እንድናደርገው የነገረንን ሳናደርግ ስንቀር ነው፡፡እንዲሁም እግዚአብሔር የማይወደውን ስናደርግ ነው፡፡**
ሮሜ 1:32; ያዕቆብ 2:10-11; ያዕቆብ 4:17; 1ኛ ዮሐ 3:4

**Q.28** የትኛውም ሐጢያት* ምን ይገባዋል?
**A. ማንኛውም ሐጢያት*** የእግዚአብሔር ቁጣ እና ቅጣት ይገባዋል፡፡
ዘዳግም 27:26; ሮሜ 1:18; ሮሜ 6:23; ኤፌ 5:6

**Q.29** የመጀመሪያ ወላጆቻችን ሐጢያት* ምን ነበር?
**A. እግዚአብሔር እንዳይበሉ የነገራቸውን ፍሬ በሉ፡፡**
ዘፍጥረት 2:16-17; ዘፍጥረት 3:6

**Q.30** ሐጢያት* እንዲሰሩ የፈተናቸው ማን ነው?
**A. ዲያቢሎስ* ሔዋንን ፈተናት ፤እሷም ፍሬውን ለአዳም ሰጠችው፡፡**
ዘፍጥረት 3:1-5; ዮሐ 8:44; 2ኛ ቆሮ 11:3; ራዕይ 12:9

**Q.31** የመጀመሪያ ወላጆቻችን ሐጢያት በሰሩ ጊዜ በዓለም ላይ ምን ሆነ?
**A. እግዚአብሔር በምድር ላይ እርግማንን ተናገረ፡፡እግዚአብሔር እንዳስጠነቀቃቸው፤ሞት ወደ ዓለም መጣ፡፡**
ዘፍጥረት 2:15-17; ዘፍጥረት 3:16-17

**Q.32** የመጀመሪያ ወላጆቻችን ሐጢያት ሲሰሩ ምን ሆኑ?
A. **እግዚአብሔር አዳም እና ሄዋንን ከገነት አስወጣቸው፡፡**ከዚያ በኋላ ቅዱስ* እና ደስተኛ አይሆኑም፡፡
ዘፍጥረት 3:8-13; 16-19; 23

**Q.33** አዳም ሐጢያት በመስራቱ ምክንያት፤ከእሱ በኋላ በኖሩት ላይ ምን ሆነባቸው?
A. **ከአዳም እና ሄዋን በኋላ የተወለዱት ሁሉ ሐጢያተኛ* ሆኑ፡፡**
መዝ 51:5; ሮሜ 5:18-19; 1ኛ ቆሮ 15:21-22

**Q.34** እግዚአብሔር ከእርግማን በታች የሆነውን ዓለምን ተዋት? እሱ ህዝቡን ከሐጢያታቸው ጋር ተዋቸው?
A. **አልተዋቸውም፤** እግዚአብሔር ሊድናቸው መረጠ፡፡እግዚአብሔር አዳኝ* ሊልክ ቃል ገባ፡፡
ማቴ 1:21; ዮሐ 3:16-17; 1 ዮሐ 4:14

**Q.35** ቃል ኪዳን* ምንድ ነው?
A. ቃል ኪዳን በሁለት ወይም ከዛ በላይ ባሉ ሰዎች መካከል ጠንካራ የሆነ የቃል መግባት ነው፡፡

**Q.36** እግዚአብሔር ከእስራኤል* ህዝብ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን ምን ነበር?
A. እግዚአብሔር የአብርሃምን ቤተሰብ ታላቅ ህዝብ ሊያደርገው ቃል ገባ፡፡ሁሉንም ህዝብ በአብርሃም በኩል ሊባርክ ቃል ገባ፡፡

እግዚአብሔር ለሙሴ ህግ ሰጠው፡፡ከሙሴ ጋር ሊሆን እና እሱን የሚታዘዙ እና የሰጣቸውን ህግጋት የሚጠብቁ ከሆነ እስራኤልን ሊባርክ ቃል ገባ፡፡

እግዚአብሔር ከልጆቹ አንዱ ታላቅ ንጉስ እንደሚሆን እና ለዘለዓለም እንደሚገዛ ለዳዊት ቃል ገባ፡፡

እግዚአብሔር አንድ ቀን አዲስ ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ ቃል ገባ፡፡የሰዎችን ሐጢያት ይቅር እንደሚል እና ልባቸውን እንደሚቀይር ቃል ገባ፡፡
ዘፍጥረት 12:1-3; ዘፍጥረት 15; ዘጸአት 24:3-7; 2ኛ ሳሙ 7:16;ኤር 31:31-34

## አስርቱ ትዕዛዛት

**Q.37** አስርቱ ትዕዛዛት ምንድ ናቸው?

**A.** አስርቱ ትዕዛዛት ለእስራኤል* ህዝብ ለሙሴ የሰጣቸው ቃላት ናቸው፡፡እግዚአብሔር እራሱ በሁለት ጽላት ላይ የጻፋቸው ናቸው፡፡

ዘጸአት 31:18; ዘዳግም 9:10

**Q.38** እነዚያ ትዕዛዛት ምንድ ናቸው?

**A.** ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።
ለራስህ ጣኦት* አታድርግ እንዲሁም አታምልክ*።
የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ።
የሰንበትን* ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።
አባትህንና እናትህን አክብር*።
አትግደል።
አታመንዝር*።
አትስረቅ።
በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።
የባልንጀራህን የሆነውን ማንኛውንም ነገር አትመኝ።

ዘጸአት 20:1-17

**Q.39** የመጀመሪያው ትዕዛዝ ምንድ ነው?

**A.** የመጀመሪያው ትዕዛዝ፤ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑል የሚለው ነው፡፡

ዘጸአት 20:3; ኢሳ 45:5-6

**Q.40** የመጀመሪያው ትዕዛዝ የሚያስተምረው ምንድ ነው?

**A.** የመጀመሪያው ትዕዛዝ የሚያስተምረው እግዚአብሔርን ብቻ እንድናመልክ* ነው፡፡

መዝ 44:20-21; ማቴ 4:10; ራዕይ 22:8-9

**Q.41** ሁለተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?

**A.** ሁለተኛው ትዕዛዝ፤ለራስህ ጣኦት* አታድርግ እንዲሁም አታምልክ* የሚለው ነው።

ዘጸአት 20:4-6; ዘዳግም 5:8-10

**Q.42** ሁለተኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረው ምንድ ነው?

**A.** ሁለተኛው ትዕዛዝ ጣኦታትን* ወይም የተቀረጸ ምስል እንዳናመልክ ያስተምረናል፡፡

ኢሳያስ 44:10-11; ኢሳያስ 46:5-9; ሐዋ 17:29

**Q.43** ሦስተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** ሦስተኛው ትዕዛዝ፤የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለው ነው።
ዘጸአት 20:7; ዘዳግም 5:11

**Q.44** ሦስተኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረው ምንድ ነው?
**A.** ሦስተኛው ትዕዛዝ የእግዚአብሔርን ስም እሱን በማያከብር* መንገድ እንዳንጠቀም ያስተምረናል፡፡
ኢሳያስ 8:13; መዝ 138:2; ራዕይ 15:3-4

**Q.45** አራተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** አራተኛው ትዕዛዝ፤የሰንበትን* ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ የሚለው ነው።
ዘጸአት20:8-11; ዘዳግም 5:12-15

**Q.46** አራተኛው ትዕዛዝ የሚስተምረን ምንድ ነው?
**A.** አራተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔርን በእረፍታችን፤በስራችን እና በአምልኳችን እንድናከብር* ያስተምረናል፡፡
ዘጸአት 16:23; ኢሳያስ 58:13-14

**Q.47** አምስተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** አምስተኛው ትዕዛዝ፤አባትህንና እናትህን አክብር* የሚለው ነው።
ዘጸአት 20:12; ዘዳግም 5:16

**Q.48** አምስተኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረው ምንድ ነው?
**A.** አምስተኛው ትዕዛዝ ወላጆቻችንን እንድንወድ እና እንድናከብር ያስተምረናል፡፡
ምሳሌ 1:8; ኤፌ 6:1-3; ቆላ 3:20

**Q.49** ስድስተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** ስድስተኛው ትዕዛዝ አትግደል የሚለው ነው።
ዘጸአት 20:13; ዘዳግም 5:17

**Q.50** ስድስተኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረን ምንድ ነው?
**A.** ስድስተኛው ትዕዛዝ ሌሎችን ሰዎች እንዳንጠላ ወይም ሰውን እንዳንገድል ያስተምረናል፡፡
ዘፍጥረት 9:6; **ማቴ** 5:21-22; 1ኛ ዮሐ 3:15

**Q.51** ሰባተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** ሰባተኛው ትዕዛዝ አታመንዝር* የሚለው ነው፡፡
ዘጸአት 20:14; ዘዳግም 5:18

**Q.52** ሰባተኛው ትዕዛዝ የሚስተምረው ምንድ ነው?
**A.** ሰባተኛው ትዕዛዝ ባል ወይም ሚስት ካልሆነን ሰው ጋር ምንም አይነት ጾታዊ ግንኙነት እንዳናደርግ ያስተምረናል፡፡
ማቴዎስ 5:27-28; ኤፌ 5:3-4

**Q.53** ስምንተኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** ስምንተኛው ትዕዛዝ አትስረቅ የሚለው ነው፡፡
ዘጸአት 20:15; ዘዳግም 5:19

**Q.54** ስምንተኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረን ምንድ ነው?
**A.** ስምንተኛው ትዕዛዝ የሰዎች የሆኑትን ነገሮች እንዳንወስድ ያስተምረናል፡፡
ዘጸአት 23:4; ምሳሌP 21:6-7; ኤፌ 4:28

**Q.55** ዘጠነኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** ዘጠነኛው ትዕዛዝ፤በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር የሚለው ነው።
ዘጸአት 20:16; ዘዳግም 5:20

**Q.56** ዘጠነኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረን ምንድ ነው?
**A.** ዘጠነኛው ትዕዛዝ ታማኝ እና እውነትን እንድንናገር ያስተምረናል፡፡
መዝ 15:1-3; ምሳሌ 12:17; 1ኛ ቆሮ 13:6

**Q.57** አስረኛው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** አስረኛው ትዕዛዝ፤የባልንጀራህን የሆነውን ማንኛውንም ነገር አትመኝ የሚለው ነው።
ዘጸአት 20:17; ዘዳግም 5:21

**Q.58** አስረኛው ትዕዛዝ የሚያስተምረው ምንድ ነው?
**A.** አስረኛው ትዕዛዝ ባለን ነገር ደስተኛ* እንድንሆን ያስተምረናል፡፡
ፊሊ 4:11; 1ኛ ጢሞ 6:6; ዕብ 13:5

**Q.59** የአይሁድ ህዝብ እግዚአብሔር ለሙሴ ለሰጠው ህግጋት ታዘዙ?
**A. አልታዘዙም፡፡የእግዚአብሔርን ህግ አፈረሱ እናም እንዳስጠነቀቃቸው እግዚአብሔር ቀጣቸው፡፡**
ዘዳግም 9:12, ሕዝ 39:23

**Q.60** ማንኛውም ሰው በማንኛውም መንገድ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅ ይችላልን?
**A. አዳም እግዚአብሔርን አልታዘዘም፡፡ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፤ማንም ሰው በማንኛውም መንገድ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ አልቻለም፡፡**
መክብብ 7:20; ሮሜ 3:23; ያዕቆብ 2:10

**Q.61** አስርቱ ትዕዛዛት የሚያሳን ምንድ ነው?
**A.** አስርቱ ትዕዛዛት እግዚአብሔር ቅዱስ እና መልካም እንደሆነ ያስተምረናል፡፡ለእግዚአብሔር እና ለባልንጀራችን እንዴት ፍቅር ማሳየት እንደምንችል ያስተምረናል፡፡እኛ ሐጢያተኞች* እና እግዚአብሔርን እንደማንታዘዝ ያስተምሩናል፡፡አዳኝ* እንደሚያስፈልገን ያስተምሩናል፡፡
መክብብ 12:13; 1ኛ ጢሞ 1:8-9; ሮሜ 3:20; 5:13; 7:7-11; ገላ 3:19-24

## ክፍል ሦስት
## ክርስቶስ እና ደህንነት*

**Q.62** አዳኝ* ማን ነው?
**A. የሐጢያተኞች* ብቸኛ አዳኝ*** ጌታ* ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
ሉቃስ 2:11; ሐዋ 4:11-12; 1ኛ ጢሞ 1:15

**Q.63** ኢየሱስ ማን ነው?
**A. ኢየሱስ ዘለዓለማዊ* የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡**
ዮሐ 1:1,14,18; ዮሐ 3:16,18; ገላ 4:4; ቆላ 1:15-18;
ዕብ 1:1-3; 1ኛ ዮሐ 5:20

**Q.64** እግዚአብሔር ልጁን ለምን ወደ ዓለም ላከው?
**A.** እግዚአብሔር ልጁን የላከው ስለሚወደን ነው፡፡እሱ ልጁን የላከው የምህረት እና የጸጋ* አምላክ ስለሆነ ነው፡፡
መዝ 103:8-11; ዮሐ 3:16-17; ሮሜ 5:7-8; ኤፌ 2:4-5; 1ኛ ዮሐ 4:9-10

**Q.65** ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርም ሰውም ነበር?
**A. አዎ፤** ኢየሱስ ፍጹም እግዚአብሔር እንዲሁም ፍጹም ሰው ነበር፡፡
ዮሐ 1:1-3, 14; ፊሊ 2:5-11; ቆላ 2:9; ዕብ 2:14-18

**Q.66** አዳኙ* ኢየሱስ ምን ሥራ ሰራ?
**A. እሱ ለእግዚአብሔር በሁሉም መንገድ ታዘዘ፤የሐጢያተኞችም* ቅጣት ተቀበለ፡፡**
ሮሜ 8:3-4; ፊሊ 2:7-8; ዕብ 4:15; ዕብ 9:14-15

**Q.67** ኢየሱስ ለምን ሞተ?
**A. ኢየሱስ በሐጢያቶች* ቦታ በመሞት የእግዚአብሔርን ቁጣ ከለከለ፡፡**
ማር 10:45; 2ኛ ቆሮ 5:19-21; ገላ 3:13

**Q.68** የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ልጅ በሐጢያተኛች* ፋንታ ለምን መከራ ሊቀበል ቻለ?
**A.ኢየሱስ፤የእግዚአብሔር ልጅ፤ሰው ሆነ፡፡**
ዮሐ 1:14; ገላ 4:4,5; ቆላ 2:9

**Q.69 የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት ሰው ሆነ**?
**A. እሱ በመንፈስ ቅዱስ ተጸነሰ*** በድንግል ማሪያም ተወለደ፡፡
ኢሳ 7:14; ማቴ 1:18-21

**Q.70** ኢየሱስ በምድር ላይ የኖረው ህይወት ምን አይነት ነው?
**A. ቀላል፤የተቀደሰ እና ትሁት የሆነ ህይወት፡፡**
ማቴ 8:20; ማቴ 11:28-30; ሉቃ 4:18-19; 2ኛ ቆሮ 8:9;2ኛ ቆሮ 10:1

**Q.71** ጌታ* ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያት* ሰርቶ ያውቃል?
**A. አያውቅም**፤እሱ ቅዱስ እና ንጹህ ነበር፡፡
ዮሐ 8:29; 2ኛ ቆሮ 5:21; ዕብ 7:26; 1ኛ ጴጥ 2:21-23

**Q.72** ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ሞት ምን አይነት ነበር?
**A. ኢየሱስ በመስቀል*** **ላይ ሞተ፡፡**
ሉቃስ 23:33; ገላ 3:13; ፊሊ 2:8

**Q.73** ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በመቃብር ውስጥ ቀረ?
**A. አልቀረም**, ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሳ፡፡
ማቴ 28:5-7; ሉቃስ 24:5-8; ሮሜ 4:25; 1ኛ ቆሮ 15:3,4

**Q.74** እግዚአብሔር ከሐጢያት* እዳቸው የሚያድናቸው እነማንን ነው?
**A. እግዚአብሔር ስለ ሐጢያቸው* ንስሃ የሚገቡትን* ያድናቸዋል፡፡እንዲሁም በጌታ* ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን፡፡**
ማር 1:14,15; ዮሐ 3:16-18; ሐዋ 20:21

**Q.75** ንስሃ መግባት* ማለት ምን ማለት ነው?
**A. ንስሃ መግባት* በሐጢያቴ አዝናለሁ፤ከሐጢያቴም እመለሳለሁ ምክንያቱምእግዚአብሔርን ያሳዝናልና ማለት ነው፡፡**
ሉቃ 19:8-10; 2ኛ ቆሮ 7:9-10; 1ኛ ተሰ 1:9-10

**Q.76** በክርስቶስ ማመን ወይም እምነት* መያዝ ማለት ምን ማለት ነው ?
**A. በክርስቶስ እምነት* መኖር ማለት በኢየሱስ ማመን ማለት ነው፡፡ያድነን ዘንድ የምንታመነው* እሱን ብቻ ነው፡፡**
ዮሐ 14:6; ሐዋ 4:12; 1ኛ ጢሞ 2:5; 1ኛ ዮሐ 5:11-12

**Q.77** በራስህ ኃይል ንስሃ መግባት* እና በክርስቶስ ማመን ትችላለህን?
**A. አይደለም**, የመንፈስ ቅዱስ* እርዳታ ያስፈልገኛል፡፡
ኤር 13:23; ዮሐ 3:5-6; ዮሐ 6:44; 1ኛ ቆሮ 2:14

**Q.78** ሰዎች ስለ ክርስቶስ እውነት የሚሰሙት የት ነው?
**A. አዳኙን* ለሁሉም ህዝብ የሚያቀረበው ፤የምስራች ዜና በሆነው በወንጌል* ውስጥ ነው፡፡**
ማር 1:1; ሐዋ 15:7; ሮሜ 1:16-17

**Q.79** አሁን አዳኛችን* ኢየሱስ ለእኛ ምን ሆነ?
**A. ኢየሱስ ነብያችን***፤ካህናችን እና ንጉሳችን ሆኗል፡፡
ማቴ 13:57; ዮሐ 18:37; ዕብ 1:1-3; ዕብ 5:5-6; ራዕይ 1:5

**Q.80** ኢየሱስ ክርስቶስ ነብይ* እንዴት ይሆናል?
**A. ምክንያቱም እሱ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ያሳየናል፡፡እሱን እንዴት እንደምናስደስት ያስተምረናል፡፡**
ዘዳግም 18:18; ዮሐ 1:18; ዮሐ 4:25-26; ሐዋ 3:22; 1ኛ ዮሐ 5:20

**Q.81** ኢየሱስ እንደ ነብይ* የሚያስፈልገን ለምንድ ነው?
**A. ምክንያቱም እግዚአብሔርን ያለ እሱ ልናውቅ አንችልምና፡፡**
ማቴ 11:25-27; ዮሐ 17:25-26; 1ኛ ቆሮ 2:14-16

**Q.82** ኢየሱስ ክርስቶስ ካህን እንዴት ይሆናል?
A. እሱ በእኛ ፈንታ ሞቷል እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር ይማልደናልና፡፡
መዝ 110:4; ዕብ 4:14-16; ዕብ 7:24-25; 1ኛ ዮሐ 2:1-2

**Q.83** ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ካህን የሚያስፈልገን ለምንድ ነው?
**A. ምክንያቱም ሐጢያታችን በደለኞች እና እንድናፍር አድርጎናልና፡፡**
ምሳሌ 20:9; መክብብ 7:20; ኢሳ 53:6; ሮሜ 3:10-12; ሮሜ 3:23; ያዕቆብ 2:10

**Q.84** ኢየሱስ እንደ ንጉስ እንዴት ይሆናል?
**A.** እሱ ይገዛናል እንዲሁም ይጠብቀናልና፡፡
መዝ 2:6-9; ኤፌ 1:19-23; ራዕይ 15:3-4

**Q.85** ኢየሱስ እንደ ንጉስ የሚያስፈልገን ለምንድ ነው?
**A. ምክንያቱም ደካሞች እና ፈሪዎች ስለሆንን፡፡**
2ኛ ቆሮ 12:9-10; ፊሊ.4:13; ቆላ 1:11-13; ዕብ 13:5-6; 2ኛ ጢሞ 1:12

**Q.86** በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን የምንቀበላቸው በረከቶች* ምንድ ናቸው?
**A. እግዚአብሔር ይቅር* ይለናል እንዲሁም ጻድቅ* ብሎ ይጠራናል፡፡**
እግዚአብሔር እንደ ውድ ልጆቹ በቤተሰቡ ውስጥ ይቀበለናል፡፡
እግዚአብሔር በልባችን* እና በባህሪያችን ቅዱስ* አድርጎናል፡፡
እግዚአበሔር በትንሳኤ* በስጋች እና ነፍሳችን ፍጹማን አድርጎናል፡፡
ሮሜ 5:18; ገላ 4:4-6; ኤፌ 1:5; ዕብ 10:10-14; 1ኛ ዮሐ 3:2

**Q.87** እነዚህን በረከቶች* እግዚአብሔር የሚሰጠኝ በራሴ መልካም ባህሪ ስላገኘዋቸው ነውን?
**A. አይደለም፤**እግዚአብሔር እነዚህን በረከቶች የሚሰጠኝ በጸጋው* ነው፡፡
እኔ አይገቡኝም እናም አልገዛዋቸውም፡፡
ኢሳ 64:6; ኤፌ 2:8-9; ቲቶ 3:4-7

**Q.88** እግዚአብሔር በእውነት ንስሃ ከገቡ* እና ካመኑ ሰዎች ላይ እነዚህን በረከቶች* ያስወግድባቸዋልን?
**A. አያስወግድባቸውም፤**ኢየሱስ እንደሚያድናቸው* የታመኑትን መቼም አይተዋቸውም፡፡
ዮሐ 10:27-30; ሮሜ 8:38-39; ፊሊ 1:6; 1ኛ ጴጥ 1:3-5

**Q.89** የእግዚአብሔር ጸጋ* ምንድ ነው?
**A.** የእግዚአብሔር ጸጋ* በማይገባን ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅር እና የእሱ በጎነት ነው፡፡
ዘጸአት 34:6; ኤፌ 1:7-8; 2ኛ ቆሮ 8:9

## ክፍል አራት
## መንፈሱ እና ቤተክርስቲያን

**Q.90** ኢየሱስን አዳኝ አድርገው ለሚታመኑት ሁሉ የእግዚአብሔር መሻት ምንድ ነው?
**A. እሱ በልባቸው* እና በባህሪያቸው ቅዱስ እንዲሆኑ ይፈልጋል።**
ኤፌ 1:4; 1ኛ ጴጥ 1:15; 2ኛ ቆሮ 7:1

**Q.91 እግዚአብሔር በልባችን* እና በባህሪያችን ቅዱስ የሚያደርገን እንዴት ነው?**
**A. እግዚአብሔር አዲስ ልብ* ይሰጠናል።እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል።**
ሕዝ 36:26; ሮሜ 8:1-14; ገላ 5:22-26; ኤፌ 1:13

**Q.92** መንፈስ ቅዱስ* ማን ነው?
**A.** መንፈስ ቅዱስ* እግዚአብሔር ነው።እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ መንፈስ ቅዱስን* ላከ።
ማቴ 28:19; ዮሐ 14:26, ዮሐ 15:26; 2ኛ ቆሮ 13:14

**Q.93** አሁን መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ምንድ ነው?
A. መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ ነው፤ጓደኛ ነው፤እናም በኢየሱስ የሚታመኑትን ሁሉ ይመራቸዋል።
ዮሐ 16:7-8,12-15; ሮሜ 8:14-16; 1ኛ ቆሮ 6:19; ኤፌ 1:14

**Q.94** መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ* እያደረገኝ እንደሆነ በምን አውቃለሁ?
**A. አዳኜን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መምሰል አድጋለሁ።የመንፈስ ቅዱስን ፍሬዎች በልቤ*** እና በባህሪዬ **ላይ አያለሁ።**
ቆላ 1:9-12; ኤፌ 3:16

**Q.95** የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች?
**A. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች** ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።
ገላ 5:22-23

**Q.96** ኢየሱስን የምትከተል ከሆነ ሁልጊዜ ትበለጽጋለህን*?
**A. አይደለም**፡፡ አንዳንድ ጊዜ ችግሮች ሊያጋጥሙኝ ይችላሉ፡፡አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ እንደሆነው መከራ ልቀበል ወይም ልጠላ እችላለሁ፡፡
ዮሐ 15:18-19; 2ኛ ጢሞ 3:12; ሮሜ 8:23-25; ያዕ 1:2-4; 1ኛ ጴጥ 4:12-13

**Q.97** በችግርህ ጊዜ እግዚአብሔር የሚረዳህ እንዴት ነው?
**A. እሱ ሊያጽናናኝ መንፈሱን ይሰጠኛል፡፡እንድትንከባከበኝ ቤተክርስቲያንን ይሰጠኛል፡፡ለእኔ ጥቅም እና ለእሱ ክብር በሁሉም ነገሮች ይሰራ ዘንድ የተስፋ ቃሉን ይሰጠኛል፡፡**
ሮሜ 5:3-5; ሮሜ 8:18; 1ኛ ተሰ 5:11; 1ኛ ጴጥ 4:12-19;1ኛ ጴጥ 5:10

**Q.98** ዓለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን* ምንድ ናት?
**A.** ዓለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን* የተሰራችው በሁሉም በእግዚአብሔር በተዋጁ* ህዝቦች ነው፡፡ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር አብ ቤተሰብ ናት፡፡መንፈስ* ቅዱስ* የሚኖርበት ቦታ ነው፡፡
1ኛ ቆሮ 12:27; ኤፌ 3:14-15; ኤፌ 5:23; ቆላ 1:24;ዕብ 2:11

**Q.99** አጥቢያ ቤተክርስቲያን* ምንድ ነው?
**A.** አጥቢያ ቤተክርስቲያን* በኢየሱስ የሚታመኑ እና ትምህርቱን የሚታዘዙ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡እነሱ በአንድነት መጽሐፍ ቅዱስን ይሰማሉ እንዲሁም ይማራሉ፡፡እርስ በእርሳቸው ይተሳሰባሉ፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት አድጎ ለማየት በአንድነት ይጸልያሉ እንዲሁም ይሰራሉ፡፡አማኞችን ያጠምቃሉ፤የጌታን እራት ይወስዳሉ፡፡
ማቴ 28:19-20; ሐዋ 2:41-42; ሐዋ 8:36-39; ሐዋ 14:23; ሮሜ 6:1-5;1ኛ ቆሮ 11:23-26; ቲቶ 1:5

**Q.100** የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አካል መሆን አለብህን?
**A. አዎ፡፡**አጥቢያ ቤተክርስቲያን በእምነቴ እንዳድግና ጠንካራ ሆኜ እንድቆም የሚረዳኝ ማህበረሰብ ነው፡፡ የኢየሱስን አዲስ ትዕዛዝ የምማርበት ቦታ ነው፡፡
ዕብ 10:24-25

**Q.101** ኢየሱስ ለቤተክርስቲያን የሰጠው አዲስ ትዕዛዝ ምንድ ነው?
A. ኢየሱስም እንዲህ አለ፤"እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ፡፡እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በእርስ ተዋደዱ፡፡"
ዮሐ 13:34

**Q.102** ይህንን ፍቅር እረስ እርሳችን እንዴት እናሳያለን?
A. ይህንን ፍቅር እርስ በእርስ ቸር ስንሆን እናሳያለን፡፡እርስ በእርስ ስንከባበር* ስንረዳዳ፤እና ከራሳችን ፍላጎት ይልቅ ሌሎችን ስናስቀድም ይህንን ፍቅር እናሳያለን፡፡
ሮሜ 12:10; ኤፌ 4:32; ቆላ 3:9,13; 1ኛ ተሰ 4:18; ያዕቆብ 5:16

**Q.103** ጥምቀት* ምንድ ነው*?
**A.** ጥምቀት* የቤተክርስቲያን መሪ ለአፍታ አንድን ሰው ውሃ ውስጥ ሲጨምር ነው፡፡ከዛም ከውኃ ውስጥ ያወጣዋል፡፡ይህን በአብ፤በወልድ፤በመንፈስ ቅዱስ* ስም ያደርጉታል፡፡
ማቴ 3:6,16; ማር 1:5; ሐዋ 8:12

**Q.104** መጠመቅ* የሚችልው ማን ነው?
**A. ጥምቀት* ለሐጢያታቸው ንስሃ ለገቡ* ሁሉ ነው፡፡ለደህንነት* በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ ነው፡፡**
ሐዋ 2:38,39; ሐዋ 8:36-37; ሐዋ 16:30-33

**Q.105** ጥምቀት* ማለት ምን ማለት ነው?
A. ጥምቀት* የአማኝ ከክርስቶስ ጋር ያለው ህብርት ምልክት ነው፤በሞተ፤በተቀበረ እና ከሞት በተነሳ ጊዜ፡፡የእሱ ቤተክርስቲያን አካል ነኝ ማለት ነው፡፡
ሐዋ 16:30-33; ሮሜ 6:3-5; ቆላ 2:12

**Q.106** ክርስቲያኖች እንዴት እርስ በእርስ የክርስቶስን ሞት ያስባሉ?
**A. በጌታ እራት በአንድነት እንካፈላለን፡፡**
ማር 14:22-24; 1ኛ ቆሮ 11:23-29

**Q.107** የጌታ እራት* ምንድ ነው?
A. የጌታ እራት* የምንበላው ዳቦ እና የምንቀምሰው ፅዋ ነው፡፡ይህን የምናደርገው የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት ለማስታወስ ነው፡፡
ማር 14:22-24; 1ኛ ቆሮ 11:23-29

**Q.108** ዳቦው ምን ማለት ነው?
**A. የተቆረሰው ዳቦ ስለ ተቆረሰው የኢየሱስ ስጋ ይናገራል፡፡እሱ አንድ ጊዜ* ለሐጢያታችን ሞቷል፡፡**
ማቴ 26:26; 1ኛ ቆሮ 11:24

**Q.109** ጽዋው ምን ማለት ነው?
**A. ጽዋው ስለ ክርስቶስ ደም ይናገራል፡፡እሱ አንድ ጊዜ ለደህንነታችን* ደምቷል፡፡**
ማቴ 26:27-28; 1ኛ ቆሮ 11:25; ዕብ 9:26-28

**Q.110** የጌታን* እራት የሚወስደው ማ ነው?
A. የጌታን* እራት በሐጢያታቸው ንስሃ* ለሚገቡ ሁሉ ነው፡፡ለደህንነት* በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ 10:16,17; 1ኛ ቆሮ 11:18-29

**Q.111** ጥምቀት* እና የጌታ እራትን* ለቤተክርስቲያን* የሰጠው ማን ነው?
**A. ጌታ* ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡**
ማቴ 26:26-29; ማቴ 28:18-20

**Q.112** ኢየሱስ ጥምቀት* እና የጌታ እራትን* ለቤተክርስቲያን* ለምን ሰጠ?
**A. ኢየሱስ እነዚህን የሰጠው ህዝቡ የራሱ እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡እነዚህ ተግባሮች ኢየሱስ ለእኛ ያደረገውን ያስታውሰናል፡፡**ማቴ 28:19; ሮሜ 6:1-5; 1ኛ ቆሮ 11:23-26

**Q.113** የኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ለቤተክርስቲያን* የሰጠው የመጨረሻው ትዕዛዝ ምንድ ነው?
**A.** ሥልጣን ሁሉ በሰማይና* በምድር ተሰጠኝ።እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ* ስም እያጠመቃችኋቸው*፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"
ማቴ 28:18-20

**Q.114** የጌታ* ቀን ምንድ ነው?
**A.** የጌታ* ቀን የሳምንቱ ቀን ነው፡፡የቀደሙት ክርስቲያኖች ተሰብስበው በዚያ ቀን ያመልኩ ነበር፡፡
ሐዋ 20:7; 1ኛ ቆሮ 16:2; ራዕይ 1:10

**Q.115** የጌታ* ቀን ለምን ተባለ?
**A. ምክያቱም ያ ቀን ኢየሱስ ከሞት የተነሳበት ቀን ነው፡፡**
ማቴ 28:1-6; ሉቃ 24:1-6; ዮሐ 20:1

**Q.116** የጌታን* ቀን እንዴት ብናሳልፈው የተሻለ ነው?
**A. የእግዚአብሔር ህዝብ በአንድነት ተሰብስቦ በማምለክ እና እርስ በእርስ በእምነታችን በመበረታታት* የጌታን* ቀን ቢያሳልፍ በጣም የተሻለ ነው፡፡**
መዝ 27:4; ሮሜ 12:9-13; ቆላ 3:16

## ክፍል አምስት
## ጸሎት እና ተስፋ

**Q.117** ጸሎት ምንድ ነው?
**A.** ጸሎት እግዚአብሔርን ማናገር ማለት ነው፡፡ስለ መልካምነቱ እናመሰግዋለን፡፡ሐጢያታችንን* እንናዘዛለን፡፡እሱ የሚያስደስቱትን ነገሮች እንጠይቃለን፡፡
ማቴ 6:6; ፊሊ 4:6; 1ኛ ዮሐ 5:14

**Q.118** መጸለይ ያለብን በማን ስም ነው?
**A. መጸለይ ያለብን በኢየሱስ ስም ነው፡፡**
ዮሐ 14:13-14; ዮሐ 16:23

**Q.119** መቼ እና የት ነው መጸለይ ያለብን?
**A. በማንኛውም ቦታ፤በማንኛውም ሰዓት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እንችላለን፡፡**
ማቴ 6:6; ኤፌ 6:18; ሐዋ 21:5; ቆላ 4:2

**Q.120** ኢየሱስ ስለ ጸሎት ያስተምረን ዘንድ ምን ሰጠን?
**A. ኢየሱስ የጌታን ጸሎት* ሰጥቶናል፡፡**
ማቴ 6:9-15; ሉቃስ 11:2-4

**Q.121** የጌታ* ጸሎት ምንድ ነው?
በሰማያት* የምትኖር አባታችን ሆይ፥
ስምህ ይቀደስ*፤
መንግሥትህ* ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ* እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤
እኛም ደግሞ የበደሉንን* ይቅር እንደምንል*
በደላችንን* ይቅር በለን*፤
ከክፉም* አድነን እንጂ
ወደ ፈተና አታግባን፤
መንግሥት ያንተ ናትና
ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።
ማቴ 6:9-13

**Q.122** በጌታ* ጸሎት ውስጥ ስንት ጥያቄዎች አሉ?
**A. ስድስት ጥያቄዎች አሉ፡፡**

**Q.123** የመጀመሪያው ጥያቄ ምንድ ነው?
A. "ስምህ ይቀደስ*፤."
ማቴ 6:9; ሉቃስ 11:2

**Q.124** በመጀመሪያው ጥያቄ የምንጸልየው ለምንድን ነው?
**A. ሁሉም ሰው የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግን ዘንድ እንጸልያለን፡፡**
መዝ 8:1-2; መዝ 72:18-19; መዝ 113:1-3

**Q.125** ሁለተኛው ጥያቄ ምንድ ነው?
A. "መንግሥትህ* ትምጣ፤"
ማቴ 6:10; ሉቃስ 11:2

**Q.126** በሁለተኛው ጥያቄ የምንጸልየው ለምንድ ነው?
**A. በምድር ላይ ህዝብ ሁሉ የምስራቹን ወንጌል ይሰማ እና ያምን ዘንድ እንጸልያለን፡፡ኢየሱስን እንደ ጌታ* አድርገው ይታዘዙ ዘንድ እንጸልያለን፡፡**
ዮሐ 17:20-21; ሐዋ 8:12; ሐዋ 28:30-31; ራዕይ 11:15

**Q.127** ሦስተኛው ጥያቄ ምንድ ነው?
**A.** "ፈቃድህ በሰማይ* እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤"
ማቴ 6:10

**Q.128** በሦስተኛው ጥያቄ የምንጸልየው ለምንድ ነው?
**A.** **መልአክቶች* በሰማይ* እንደሚያደርጉት በምድር ላይ ያለ ህዝብ ሁሉ እግዚአብሔር በሚፈልገው በሁሉም መንገድ እንዲያደርግ እንጸልያን፡፡**
ማቴ 103:19-22; ማቴ 143:10

**Q.129** አራተኛው ጥያቄ ምንድ ነው?
**A.** "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤"
ማቴ 6:11; ሉቃስ 11:3

**Q.130** በአራተኛው ጥያቄ የምንጸልየው ለምንድ ነው?
**A.** **እግዚአብሔር ለሰውነታችን የሚያስፈልገውን ነገሮች ሁሉ እንዲሰጠን እንጸልያለን፡፡**
መዝ 145:15-16; ምሳሌ 30:8-9; ማቴ 6:31-33

**Q.131** አምስተኛው ጥያቄ ምንድ ነው?
**A.** "እኛም ደግሞ የበደሉንን* ይቅር እንደምንል*በደላችንን* ይቅር በለን*፤"
ማቴ 6:12; ሉቃስ 11:4

**Q.132** በአምስተኛው ጥያቄ የምንጸልየው ለምንድ ነው?
**A.** **እግዚአብሔር በደላችንን* ይቅር እንዲለን* እንጸልያለን፡፡የበደሉንን ደግሞ ይቅር* ማለት እንችል ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳን እንጸልያለን፡፡**
መዝ 51:2-3; ማቴ 5:23-24; ኤፌ 4:32

**Q.133** ስድስተኛው ጥያቄ ምንድ ነው?
**A.** ከክፉም* አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤
ማቴ 6:13; ሉቃስ 11:4

**Q.134** በስድስተኛው ጥያቄ የምንጸልየው ለምንድ ነው?
**A. እግዚአብሔር ከሐጢያት* እንዲጠብቀን እንጸልያለን፡፡እንዲሁም ከክፉ* እንዲጠብቀን፡፡**
መዝ 119:11; 1ኛ ቆሮ 10:13; 2ኛ ጢሞ 4:18

**Q.135** ጸሎት ምን ያስተምረናል?
**A. ጸሎት እግዚአብሔርን ለእርዳታው ሙሉ በሙሉ እንድንታመነው* ያስተምረናል፡፡**
ኤፌ 6:18; ፊሊ 4:6; ዕብ 4:16

**Q.136** ክርስቶስ አሁን ያለው የት ነው?
**A. ክርስቶስ አሁን ያለው በሰማይ* በአባቱ በእግዚአብሔር ቀኝ ነው፡፡**
ማር 16:19; ሐዋ 5:31; ሮሜ 8:34

**Q.137** ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ዳግም ይመጣልን?
**A. አዎ**, በመጨረሻ ቀን በምድር ያሉ ህዝቦች ላይ ሁሉ ሊፈርድ ይመጣል፡፡እሱን የሚጠብቁትን ያድናቸዋል፡፡
ማቴ 25:31-32; 2ኛ ተሰ 1:7-9; 2ኛ ጢሞ 4:1; ዕብ 9:28

**Q.138** ጻድቃን* ሲሞቱ ምን ይሆናሉ?
**A. የጻድቃን ስጋዎች ወደ አፈር ይመለሳል፡፡ነፍሳቸው* ከጌታ* ጋር ይሆናል፡፡**
ዘፍጥረት 3:19; መክብብ 12:7; 2ኛ ቆሮ 5:8

**Q.139** ክፉ ሰዎች ሲሞቱ ምን ይሆናሉ?
**A. የክፉ ሰዎች ስጋዎቻቸው ወደ አፈር ይመለሳል፡፡ነፍሳቸው በቅጣት ይሰቃያሉ፡፡እግዚአብሔር በፍርድ ለሚመጣበት ቀን ይጠብቃቸዋል፡፡**
ሉቃስ 16:23-24; ዮሐ 5:28-29; 2ኛ ጴጥ 2:9

**Q.140** ሙታን እንደገና በህይወት ሊኖሩ ይነሳሉን?
**A. አዎ**፤ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ሁሉም የሞቱት ይነሳሉ፡፡
ዳንኤል 12:2; ዮሐ 5:28-29; ሐዋ 24:14-15

**Q.141** ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመጣበት ቀን በክፉ ሰዎች ላይ ምን ይሆናል?
**A. እግዚአብሔር ማለቂያ በሌለው ጥፋት በሲኦል* ውስጥ የቀጣቸዋል፡፡ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ህልውና ውጪ ይጣላሉ፡፡**
ማቴ 25:41,46; ማር 9:47,48; ሉቃስ 12:5; ሉቃስ 16:23-26; 2ኛ ተሰ 1:9; ራዕይ 20:12-15

**Q.142** በጻድቃን* ላይ ምን ይሆናል?
**A. ጻድቃን በደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራሉ፡፡እነሱ ለዘለዓለም በአዲስ ሰማይና* በአዲስ ምድር ይኖራሉ፡፡**
ኢሳ 66:22-23; 2ኛ ጴጥ 3:13; ራዕይ 21:2-4

**Q.143** አዲሱ ሰማይና* ምድር ምን ይመስላሉ ?
**A. በአዲሲቱ ሰማይና ምድር ከእግዚአብሔር ጋር እንሆናለን፡፡ሐጢያትን እንሰራም፡፡እንሞትም፡፡በዚያ እርግማን አይኖርም፡፡በዚያ ሀዘንና ህመም አይኖርም፡፡ጥፋተኛ እንሆንም፤እንፈራም ወይም አናፍርም፡፡ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣውን ደስታ እናውቃለን፡፡**
ዕብ 12:22-23; ይሁዳ 24; ራዕይ 21:1-5; ራዕይ 22:1-4.

# የቃላት ዝርዝር

| **ቃል** | **ማብራሪያ** |
|---|---|
| ማደጎ | ማደጎ አንድን ሰው ወደ አንድ ቤተሰብ የሚያመጣ ህጋዊ ተግባር ነው፡፡ያ ሰው አሁን እንደ ልጅ ሆኗል፡፡ ቀድሞ፤ለእግዚአብሔር እንግዶች እና የእግዚአብሔር ጠላቶች ነበርን፡፡ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር የራሱ ልጆች አድርጎ ጠርቶናል፡፡ |
| ዝሙት | ዝሙት ማለት ሚስትህ ካልሆነች ወይም ባልሽ ካልሆነ ሰው ጋር ጾታዊ ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡ |
| መልአክ | መልአክ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሲሆኑ፤ከእግዚአብሔር መልዕክቶችን ያመጣሉ፡፡መልአክ መንፈስ* ነው፡፡መልአክቶች ስለ እግዚአብሔር መልካም ነገሮችን ይናገራሉ፡፡መልአክ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ያደርጋሉ፡፡መልአክ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ላሉት መልካም ያደርጋሉ፡፡መጥፎ መልአኮች የሚሰሩት ለዲያቢሎስ* ነው፡፡ |
| ጥምቀት/ማጥመቅ | የቤተክርስቲያን* መሪ አንድን ሰው ውኃ ውስጥ ይጨምረዋል፡፡ከዚም ከውኃ ውስጥ ያወጣዋል፡፡በዚህ መንገድ ክርስቶስ ንጹህ እንዳደረገን እያሳየን ነው፡፡እንዲሁም የቤተክርስቲያን* አካል እንደሆንን ለሁሉም ሰው እያሳየን ነው፡፡ስንጠመቅ ኢየሱስ እንደሞተ ያስታውሰናል፡፡ሰዎች በመቃብር አኖሩት፡፡ነገር ግን እሱ ከሞት ተነሳ፡፡ |
| አማኝ | አማኝ ክርስቶስን የሚያውቅ እና የሚታመን ሰው ነው፡፡ |
| በረከቶች | በረከቶች እግዚአብሔር ለእኛ የሚያደርግልን መልካም ነገሮች ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን እንዲባርከን ስንጠይቀው፤እንዲረዳን እና መልካም ነገር በእኛ እንዲያደርግ እየጠየቅነው ነው፡፡ |
| መጸነስ | አዲስ ህይወት በሴቲቱ አካል ውስጥ ሲጀመር፤ህጻን እየተፈጠረ ያለበት ቅጽበት ነው፡፡ |
| ደስታ | መደሰት ማለት ባለን ነገር ደስተኛ መሆን ነው፡፡ያለን ነገር በቂ እንደሆነ ማወቅ ነው፡፡ |
| ቤተክርስቲያን | ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ የሚከተሉ እና የሚያምኑ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡በአንድነት ይሰበሰባሉ፡፡አማኞችን* ያጠምቃሉ*፡፡የጌታ እራት ይወስዳሉ፡፡የክርስቶስን ትምህርት ይታዘዛሉ፡፡ |
| መስቀል | መስቀል በእንጨት በአንድነት ተጣምሮ የተዘጋጀ ነው፡፡ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ዘመን፤ሰዎች ወንጀለኞችን ለመግደል በመስቀል ላይ ይሰቅሏቸው ነበር፡፡ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ፡፡ |
| እርግማን | በአንድ ሰው ወይም ነገር ላይ ጉዳት ወይም ቅጣት ሊያመጣ የሚችል ኃይለኛ ቃል ነው፡፡ |
| ዲያቢሎስ | ዲያቢሎስ ሌላው የሰይጣን* ስም ነው፡፡ሰይጣን ከመጥፎ መልአክቶች* እጅግ የከፋው ነው፡፡[መልአክ ይመልከቱ] |
| ደቀመዝሙር | ደቀመዝሙር ሌላ ሰው የሚከተል እና ከእሱ የሚማር ሰው ነው፡፡በኢየሱስ የሚያምን ሰው ነው፡፡የኢየሱስ የሚያስተምረውን የሚከተል ሰው ነው፡፡ |

| | |
|---|---|
| ዘለዓለማዊ | የነበሩ ወይም ሁልጊዜ የሚቀጥሉ ነገሮች ዘለዓለማዊ ናቸው፡፡መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሌለው ነገር፡፡ |
| እምነት | እምነት በአንድ ሰው ወይም በአንድ ነገር ማመን ማለት ነው፡፡በእግዚአብሔር መታመን* እና ማመን ነው፡፡ልናየው የማንችል ቢሆንም እግዚአብሔር እውነት እንደሆነ ማመን፡፡ |
| ይቅር ማለት | ይቅር ማለት ፍቅር ማሳየት እና በአንድ ሰው ላይ በደልን አለማስታወስ ማለት ነው፡፡እግዚአብሔር ይቅር ሲለን፤እኛ የሰራናቸውን መጥፎ ነገሮች አይቆጥርብንም፡፡ |
| ክብር | የእግዚአብሔር ክብር እንደ አንድ ታላቅ ንጉስ፤እግዚአብሔርን ቆንጆ እና ታላቅ የሚደርገው ነው፡፡ |
| ጸጋ | ጸጋ በሰራናቸው ሐጢያት ምክንያት ልናገኘው የማንችልው እግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ ጸጋ እግዚአብሔር ለእኛ ቸር ከመሆኑ የተነሳ የሰጠን ነው፡፡ይቅርታ* እና እርዳታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣሉ፡፡ |
| ልብ | ልብ የአንድ ሰው እጅግ አስፈላጊው ክፍል ነው፡፡ነገሮችን የሚሰማው፤የሚያስበው እና የሚወስን የአንድ ሰው ክፍል ነው፡፡ |
| ሰማይ | ሰማይ እግዚአብሔር እና ክርስቶስ ያሉበት ስፍራ ነው፡፡እግዚአብሔር በዚያ ይኖራል እንዲሁም ይገዛል፡፡ሰማይ እግዚአብሔርን እና ክርስቶስን በእውነት የሚያውቁ ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበት ስፍራ ነው፡፡ሰዎች ሁልጊዜ ደስተኞች የሚሆኑበት እና ያለምንም ችግር የሚኖሩበት ቦታ ነው፡፡አዲሲቱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር እግዚአብሄርን የሚያውቁ የወደፊቱ ቤት ነው፡፡ |
| ሲኦል | ሲኦል እግዚአብሔር ሐጢያተኞችን ከእራሱ የሚለይበት ስፍራ ነው፡፡ሲኦል ሐጢያተኞች ከሞት በኋላ የሚቀጡበት ስፍራ ነው፡፡ |
| ቅዱስ | ቅዱስ መሆን ማለት ለእግዚአብሔር መለየት ነው፡፡እግዚአብሔርን መምሰል ነው፡፡እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ነው፡፡ቅዱስ ስንሆን ያለ ሐጢያት መሆን ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ነን ማለት ነው፡፡ |
| መንፈስ ቅዱስ | ኢየሱስ ሰዎችን ይረዳ ዘንድ የላከው የእግዚአብሔር መንፈስ [መንፈስን ተመልከቱ] ነው፡፡መንፈስ ቅዱስ ሌላኛው የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ፤የክርስቶስ መንፈስ፤የሚረዳን መንፈስ ተብሎ ይጠራል፡፡መንፈስ ቅዱስ ስብዕና ነው፤ነገር ግን እንደ እኛ ሰው አይደለም፡፡እሱ እግዚአብሔር ነው፤ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል ነው[ስላሴን ይመልከቱ]፡፡በዓለም ላይ ባሉ ህዝቦች መካከል የእግዚአብሔርን ስራ ይሰራል፡፡ማንም ሰው መንፈስ ቅዱስን አያየውም ነገር ግን ኢየሱስን በሚያውቁ ሰዎች ውስጥ እና ጋር ይኖራል፡፡ |
| ክብር | አንድን ሰው ማክበር ማለት ስለ ሰውየው ደህና መናገር ነው፡፡በዚያ ሰው ዘንድ በደህና መመላለስ ነው ምክንያቱም ታከብራቸዋለህ እንዲሁም ዋጋ ትሰጣቸዋለህ፡፡ |
| መቀደስ | በደህና መኖር ነው፡፡ለእግዚአብሔር ክብር በሚያሳይ መንገድ መኖር ነው፡፡መልካም እና ትክክለኛ ነገሮችን የሚያደርግ ነው፡፡ |

| | |
|---|---|
| ጣኦት | ጣኦት ማለት ሰዎች የሚጸልዩለት ከእንጨት፤ድንጋይ ወይም ብረት የተሰራ ማንኛውም ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ* አለባቸው፡፡ጣኦት ማለት የአንድ ሰው ወይም ነገር ምስል ሆኖ ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚወዱት ነው፡፡ጣኦት ሐሰተኛ አምላክ ነው፡፡አንድ ሰው ከእግዚአብሔር አስበልጦ የሚወደው ነገር ነው፡፡ |
| እስራኤል | የአይሁድ ህዝብ የሚኖሩበት ምድር ነው፡፡የእስራኤል ህዝብ ሌላኛው የአይሁድ ህዝብ ስም ነው፡፡የአብርሃም፤ይስሃቅ እና ያዕቆብ ልጆች ናቸው፡፡ |
| አይሁዳዊ | አይሁዳዊ ከአብርሃም፤ይስሃቅ እና ያዕቆብ እንዲሁም ከልጆቻቸው የተወለደ ሰው ነው፡፡የአይሁድ እምነት* ያለው ሰው ነው፡፡ |
| መንግስት | መንግስት አንድ ንጉስ የሚገዛበት ስፍራ ነው፡፡የእግዚአብሔር መንግስት እግዚአብሔር የሚገዛው ስፍራ ነው፡፡ |
| ህግ | ህግጋት አንድ ገዢ ህዝብ እንዴት መኖር እንዳለበት ለመንገር የሚያዘጋጀው ነው፡፡እግዚአብሔር የእስራኤል ህዝብ ይተዳደርበት ዘንድ ለሙሴ ህግጋን ሰጥቷል፡፡ |
| ጌታ | ጌታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡እሱ ከሁሉም በላይ ነው፤ከሁሉም ነገሮች ገዢ በላይ ነው ማለት ነው፡፡ስንታዘዘው ለኢየሱስ የምንጠቀመው ስም ነው፡፡ |
| ነብይ | ነብይ ለሌሎች ሰዎች እግዚአብሔር የሚፈልገውን መናገር የሚችል ሰው ነበር፡፡ነብያቶች ከረጅም አመታት በፊት ለእግዚአብሔር ተናግረዋል፡፡አንድ ሰው ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ተናግሯል፡፡ |
| ስኬታማነት | መሳካት በመልካም ነገሮች መደሰት ማለት ነው፡፡ስኬታማ በመልካም ጤንነት ላይ መሆን ወይም ሃብታም መሆን ነው፡፡ሰዎች ስለእኛ መልካም ነገር ሲናገሩ ስኬታማ ነን ማለት ነው፡፡በሌሎች ሰዎች መልካምነት ስንደሰት ስኬታማ ነን ማለት ነው፡፡ |
| መዋጀት | አንድ ነገር ከጠፋ ወይም ከተወሰደ በኋላ እንደገና መልሶ መግዛት ማለት ነው፡፡የአንተ ለነበረ ነገር ዋጋ መክፈል ማለት ነው፡፡ |
| ንስሃ መግባት | ንስሃ መግባት ማለት ከሐጢያት* መመለስ ማለት ነው፡፡እግዚአብሔር እንድናደርገው የሚፈልገውን ማድረግ ነው፡፡ባለፈው ጊዜ ያደረከውን መጥፎ ነገሮች ደግሞ ላለማድረግ መወሰን ማለት ነው፡፡ |
| ማክበር | ማክበር ሰዎችን ዋጋ እንዳላቸው አድርጎ መቀበል ማለት ነው፡፡ |
| ትንሳኤ | ትንሳኤ ከሞት መነሳት ማለት ነው፡፡እንደገና ህያው መሆን ነው፡፡ |
| ጻድቅ | ጻድቅ መሆን በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛ መሆን ነው፡፡ጻድቃን በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክል የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡እግዚአብሔር አንድን ሰው ትክክለኛ ሲያደርገው፤ያ ሰው ንጹህ እንደሆነ ይመለከተዋል፡፡ጻድቅ ሰው የእግዚአብሔር ወዳጅ እንጂ ጠላቱ አይሆንም፡፡ |
| ሰንበት | ሰንበት እግዚአብሔር ከመፍጠር ስራው ያረፈበት ቀን ነው፡፡ሰንበት እግዚአብሔር ለአይሁድ* ህዝብ ስራ እንዳይሰሩ የነገራቸው ቀን ነው፡፡እግዚአብሔርን ያመለኩበት እና ያረፉበት ልዩ ቀን ነው፡፡ |

| | |
|---|---|
| መዳን/ደህንነት | ደህንነት እግዚአብሔር ከሐጢያት* ኃይል እና ውጤቶቹ ሲያድነን ነው፡፡ከመጥፎ ነገሮች መዳን ወይም ደህንነት ማግኘት ማለት ነው፡፡ |
| ሰይጣን | ሰይጣን ሌላኛው የዲያቢሎስ* ስም ነው፡፡ሰይጣን* ከመጥፎ መላዕክቶች እጅግ የከፋው ነው [መልአከት ይመልከቱ]፡፡ |
| አዳኝ | ኢየሱስ አዳኝ ነው፡፡ወደ እግዚአብሔር የሚያመጣን አንድ ሰው እንዲሁም በሰራናቸው ሐጢያቶች ከመቀጣት የሚያድነን ነው፡፡ |
| ሐጢያት/ሐጢያተኛ | ሐጢያት ማለት ሰዎች የሚያደርጉት እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ወይም ሰዎችን የሚጎዳ መጥፎ ነገሮች ናቸው፡፡እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ህግጋት በማንታዘዝ ጊዜ፤ሐጢያት አንሰራለን፡፡እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን በማናደርግ ጊዜ ሐጢያት እንሰራለን፡፡ሁሉም ሰው ሐጢያተኛ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚያሳዝንን ወይም ሰዎችን የሚጎዳ ነገሮቸን ያደርጋሉና፡፡ሁሉም ሰው ሐጢያተኛ ነው ምክንያቱም ሁሉም ከመጥፎ ምኞቶች ጋር ተፈጥሯልና፡፡ |
| ነፍስ | ነፍስ በህይወት ሳለን በእኛ ውስጥ የሚኖር እና ከሞትንም በኋላ የሚኖር ልናየው የማንችለው ነው፡፡እግዚአብሔር ለአዳም እና ለሔዋን የህይወት እስትንፋስ ሲጣቸው ነፍስን ሰጥቷቸዋል፡፡የሰው ነፍስ አንዳንድ ጊዜ የሰው መንፈስ ተብሎ ይጠራል [መንፈስን ተመልከቱ]፡፡ |
| መንፈስ | መንፈስ ስጋ የሌለውና ማንም ሊያየው የማይችል ፍጡር ነው፡፡እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡እግዚአብሔር ሌሎች ልናያቸው የማንችላቸውን እና መልካምም ክፉም መሆን የሚችሉ የመንፈስ ፍጡራንን ፈጥሯል (መልአክቶች*)፡፡የሰው ነፍስ* አንዳንድ ጊዜ የሰው መንፈስ ተብሎ ይጠራል [ነፍስ ተመልከቱ]፡፡ |
| ስላሴ | ስላሴ የእግዚአብሔርን አንድነት በሦስትነት የምንናገርበት ቃል ነው፡፡እግዚአብሔር አብ፤እግዚአብሔር ወልድ፤እና እግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ*፡፡ |
| መታመን | መታመን ማለት እውነት ብላችሁ የምታስቡትን አንድን ነገር ወይም ሰው መከተል ማለት ነው፡፡ማመን* እና፤በእምነት* መመላለስ[እምነት ተመልከት]፡፡ |
| ድንግል | ድንግል ጾታዊ ግንኙነት አድርጋ የማታውቅ ማለት ነው፡፡ |
| አምልኮ | ማምለክ ማለት እግዚአብሔር ትልቅ እንደሆነ እና በጣም እንደምንወደው ማሳየት ነው፡፡ማምለክ ማለት ለእግዚአብሔር ክብር* መስጠት እና ማመስገን ማለት ነው[ክብርን ተመልከቱ]፡፡ለእግዚአብሔር ጋር ስንሆን ልናደርገው የሚገባ ነውና፡፡ |

**እትም በ:**
www.clearandsimplemedia.org

**የዚህን መጽሐፍ ኤሌክትሮኒክ እትም ለማግኘት፤የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ፡**
www.asimpleword.org

**ስለዚህ መጽሐፍ እና ሌሎች ተመሳሳይ አቅርቦቶች ለማወቅ፤የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይመልከቱ፡**
www.clearandsimplemedia.org
**ትርጉም በ:**
www.christian-translation.com